THE MANITOBA HUMAN RIGHTS COMMISSION
LA COMMISSION DES DROITS DE LA PERSONNE DU MANITOBA

# አቤቱታ የማስገቢያ አጋዥ

*የሰብዓዊ መብቶች ኮድ (“ኮድ”)* መድልዎ ደርሶብኛል ብሎ የሚያምን ማንኛውም ሰው አቤቱታውን ለማኒቶባ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን (“ኮሚሽን”) እንዲያስገባ የሚያስችል የፕሮቪንስ ሕግ ነው። ቀጣሪዎች፣ አገልግሎት አቅራቢዎች እና አከራዮች ያለ አሳማኝ ምክንያት መድልዎ መፈጸም የለባቸውም ይላል።

## የደረሰብኝ መድልዎ ነውን?

መድልዎ ማለት አንድ ሰው ባለው *በኮዱ* የተከለለ ባሕርይ ምክንያት ያን ሰው በሚጎዳ መልኩ ያለ አሳማኝ ምክንያት **ያን ሰው ለይቶ ማየት** ነው። *በኮዱ* የተከለሉ ባሕርያት የሚባሉት ዘር ወይም ብሔር፤ ዜግነት፤ ኃይማኖት ወይም እምነት፤ ጎሳ፤ ዕድሜ፤ ጾታ (እርግዝናን ጨምሮ)፤ ጾታዊ ማንነት፤ የወሲብ ምርጫ፤ የጋብቻ ወይም የቤተሰብ ሁኔታ፤ የገቢ ምንጭ፤ ፖለቲካዊ እምነት፤ አካላዊ ወይም አእምሯዊ ጉዳት፤ ማኅበራዊ ጉዳት፤ እና የወንጀል ታሪክን የሚያካትቱ የማንነት መገለጫዎች ናቸው።

በተጨማሪም መድልዎ ማለት *በኮዱ* በተዘረዘሩት ባሕርያት ላይ የተመሠረቱ የአንድ ሰው ልዩ ፍላጎቶችን **ምክንያታዊ በሆነ መልኩ አለማስተናገድ** ነው።
በታሪክ ጉዳት የደረሰበት የሌላ ቡድን አባል በመሆን ላይ ተመሥርተው የሚደረጉ አቤቱታዎችን ኮሚሽኑ ከግብዓት ባለሙያው (ኢንቴክ ኦፊሰሩ) ጋር ተጨማሪ ውይይት ካደረገ በኋላ ሊቀበል ይችላል።

## የደረሰብኝ ጥቃት ነውን?

ጥቃት የመድልዎ አይነት ነው። ጥቃት ማለት በኮዱ ከተዘረዘሩ ባሕርያት (መገለጫዎች) ጋር በተያያዘ የሰውን ክብር የሚነካ ተደጋጋሚ የሆነ ድርጊት በአንድ ሰው ላይ ሲደርስ ሲሆን ወሲባዊ ጥቃትን ያካትታል።

## የደረሰብኝ ቂም በቀል ነውን?

ቂም በቀል ማለት አንድ ሰው አቤቱታ በማስገባቱ፣ በአቤቱታ ሂደቱ በመሳተፉ ወይም *ኮዱን* ለመቃረን ፈቃደኛ ባለመሆኑ ምክንያት የሚደርስበት በቀል ነው።

## ማንም ሰው አቤቱታ ማስገባት ይችላልን? የጊዜ ገደብ አለውን?

ማንም ሰው ሌላ ሰው *ኮዱን* ጥሷል ብሎ የሚከስስ አቤቱታ ማስገባት ይችላል። አቤቱታዎች ተፈጽሟል የተባለው የመድልዎ ድርጊት በተፈጸመ በአንድ (1) ዓመት ጊዜ ውስጥ መመዝገብ አለባቸው። አንዳንድ ጊዜ ይህ የጊዜ ገደብ ሊራዘም ይችላል።

## አቤቱታ ማስገባት የምችለው እንዴት ነው?

መድልዎ ደርሶብኛል የሚል እምነት ካለዎ እባክዎ ኮሚሽኑን ያግኙ እና ከግብዓት ባለሙያ ርዳታ ያገኛሉ። አገልግሎቶቻችን እና ሕትመቶቻችን በፈረንሳይኛ እና በእንግሊዝኛ የሚገኙ ሲሆኑ አካላዊ ጉዳት ያለባቸው

ሰዎችም መጠቀም እንዲችሉ ተደርገው የተዘጋጁ ናቸው። በተጨማሪም ጥያቄ ከቀረበልን ተርጓሚም ማቅረብ እንችላለን። የሰብዓዊ መብት አቤቱታ ለማቅረብ ወይም ከሰብዓዊ መብት ጥሰት ጋር በተያያዘ ምክር ለማግኘት የሚከፈል ክፍያ የለም።

የኮሚሽን ሠራተኞች ከወገንተኝነት የጸዱ እና ከሁለቱ ወገኖች ለየትኛውም የማይወግኑ ናቸው።

## መስጠት የሚገባኝ መረጃ ምን አይነት ነው?

ችግርዎ *በኮዱ* ሽፋን ሊያገኝ የሚችል ከሆነ የግብዓት መጠይቅ ቅጽ ይሞሉ ዘንድ በግብዓት ባለሙያ ይጠየቃሉ። ይህ ቅጽ አቤቱታዎን እናረቅቅ ዘንድ ይረዳናል። ቅጹን እና የሚሰጡንን መረጃ ተጠቅመን እርስዎ (“አቤቱታ አቅራቢ”) አቤቱታ የሚያቀርቡባቸውን ድርጅት ወይም ግለሰብ (“መልስ ሰጪ”) እንለያለን። በተጨማሪም ሠራተኞች ስለ የእርስዎ የመድልዎ ክስ መረጃ (ምን ተፈጠረ፣ መድሏዊ ድርጊቱ የተደረገበት ምክንያት ብለው እርስዎ የሚያምኑት ምንድ ነው፣ ወዘተ) ይሰበስባሉ። ድርጊቱ ሲፈጸም የተመለከቱ ምስክሮች ስለመኖራቸው እና ሌሎች አቤቱታዎን የሚመለከቱ መረጃዎች (የሕክምና ማስረጃ፣ የቤት ተከራይነት ማስረጃ፣ የቼክ ስተቦች እና መሰለ የቅጥር መዝገቦች፣ ወዘተ) ሊጠየቁ ይችላሉ። በአቤቱታዎ ላይ ተመሥርቶ እኛ አቤቱታዎን ለመመርመር የሚያስፈልጉንን መረጃዎች እናገኝ ዘንድ የሕክምና እና ሌሎች የይሁንታ ቅጾችን እርስዎ እንዲፈርሙም ሊጠየቁ ይችላሉ።

አቤቱታዎን ለመመርመር የሚረዱ ሌሎች ሰነዶችን የግብዓት ባለሙያዎች ከእርስዎ ሊጠይቁ ይችላሉ። እነርሱ ይህን መረጃ በእርስዎ ፋይል ላይ ያከማቻሉ። አቤቱታዎ ከተመረመረ መርማሪው የእርስዎን አቤቱታ ለመመርመር ሊያስፈልጓቸው የሚችሉ ሰነዶችን ወይም ሌላ ማንኛውም አይነት ማስረጃ ከእርስዎ ሊጠይቁ ይችላሉ። አቤቱታዎን ይመለከታሉ ብለው እርስዎ የሚያምኗቸው ሰነዶች ወይም ሌሎች ነገሮች እርስዎ ዘንድ ካሉ ለመርማሪ ለማቅረብ ይቻል ዘንድ በጥንቃቄ ያኑሯቸው።

## አቤቱታውን የማስገባው በማን ላይ ነው?

የግብዓት ባለሙያዎቻችን ሰነዶችን (እንደ ”ቲ4” ወይም የቅጥር መዝገብ የመሳሰሉትን) በማጣራት እና የድርጅቱን ሕጋዊ ስም በማግኘት እርስዎ አቤቱታውን በማን ላይ እንደሚያስገቡ ይወስኑ ዘንድ ይረዱዎታል። *ኮዱ* የሚመለከተው የቀጣሪዎችን፣ የአገልግሎት አቅራቢዎች እና የቤት አቅራቢዎችን ድርጊት በመሆኑ አቤቱታው የሚቀርበው በድርጅት ወይም ማኅበር ላይ ነው። አንዳንድ ጊዜ አቤቱታው በግለሰብ ላይ ሊደረግ ይችላል (ለምሳሌ አንድ ግለሰብ በአንድ ቢዝነስ ባለቤት ጥቃት ደርሶበት ከሆነ ወይም የቤት አቅራቢው ግለሰብ ከሆነ)።

## ኮሚሽኑ ምክር ሊሰጠኝ ይችላልን?

የግብዓት ባለሙያዎቻችን ሕጋዊ ምክር ሊሰጡ አይችሉም። ስለ *ኮዱ*፣ ስለ መርሆቹ እና ስለ የሚሸፍናቸው ነገሮች መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ። ከልምዳቸው ተነስተው ጥቆማ ሊሰጡ ይችላሉ። ጠበቃ የማግኘት መብት አለዎት፣ አስፈላጊ ግን አይደለም። የኮሚሽን ሠራተኞች ከወገንተኝነት የጸዱ ናቸው፤ ከሁለቱ ወገኖች ለማንኛውም አይወግኑም።

## ኮሚሽኑ አቤቱታዬን ምን ያደርገዋል?

የግብዓት ባለሙያዎቻችን በግብዓት መጠይቅ ቅጹ እርስዎ የሚሰጡትን መረጃ ወስደው በመደበኛ ቅጻችን አቤቱታውን ያዘጋጃሉ። አቤቱታው የአቤቱታዎን መነሻ ምክንያት በግልጽ ማስቀመጥ የሚኖርበት ሲሆን ርዝመቱም አብዛኛውን ጊዜ 1 ወይም 2 ገጾች ብቻ ነው።
አቤቱታው ለመልስ ሰጪው ከመሰጠቱ በፊት መመዝገብ አለበት።
በመቀጠል ኮሚሽኑ አቤቱታውን መመርመር የሚችል መሆን አለመሆኑን ኮሚሽኑ ይወስናል። አንዳንድ ጊዜ አቤቱታዎች በሌላ የሕግ ሂደት አስቀድመው የታዩ ከሆኑ ወይም አቤቱታ የቀረበባቸው ድርጊቶች በ*ኮዱ* ሽፋን የሚያገኙ ካልሆኑ አቤቱታዎቹ ያለ ምርመራ ሊሰረዙ ይችላሉ። ይህን ሂደት በተመለከተ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ ያዘጋጀነውን "*የመጀመርያ ምዘና እና ያለ ምርመራ መሰረዝ አጋዥ*" ይመልከቱ።

ኮሚሽኑ አቤቱታውን በሚመረምርባቸው ጊዜያት ደግሞ የኮሚሽኑ ኤግዜኪዩቲቭ ዳይሬክተር የምርመራውን ግኝቶች ይመለከታል። ኤግዜኪዩቲቭ ዳይሬክተሩ በቂ የመድልዎ ማስረጃ እንዳለ ከወሰነ ለአቤቱታው በሚውል ለሕዝብ ክፍት የሆነ ችሎት ላይ ፈራጁ የመጨረሻ ውሳኔ ያስተላልፍ ዘንድ ኤግዜኪዩቲቭ ዳይሬክተሩ ይጠይቃል። ኤግዜኪዩቲቭ ዳይሬክተሩ የአቤቱታው ክሶች በ*ኮዱ* ሽፋን ከሚያገኙ ነገሮች ውጪ እንደሆኑ፣ በሌላ *አክት* ውሳኔ ያገኙ እንደሆኑ፣ ወይም በበቂ የመድልዎ ማስረጃ የተደገፉ እንዳልሆኑ ከወሰነ አቤቱታውን ይሰርዛል። ስለ የምርመራ ሂደቱ በቂ መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ ያዘጋጀነውን "*የምርመራ ሂደት አጋዥ*" ይመልከቱ። ስለ ለሕዝብ ክፍት የሆኑ ችሎቶች መረጃ ማግኘት ከፈለጉ ያዘጋጀነውን "*የፍርድ አጋዥ*" ይመልከቱ።

በተጨማሪም በሂደቱ የተለያዩ ጊዜያት ኮሚሽኑ የሽምግልና ሚና ለመጫወት ጥያቄ ያቀርባል። ስለ የሽምግልና ሂደቱ በቂ መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ ያዘጋጀነውን "*የሽምግልና አጋዥ*" ይመልከቱ።

## መደበኛ አቤቱታ ሳላስገባ ርዳታ ማግኘት እችላለሁን?

በችግርዎ አይነት ላይ ተመሥርቶ የኮሚሽኑ ሠራተኞች በቅድመ-አቤቱታ ሽምግልና የእርስዎን ችግር መፍታት ሊችሉ ይችላሉ። እርስዎ ከተስማሙ የኮሚሽኑ ሠራተኛ እርስዎ መድልዎ አድርሶብኛል ብለው ላመኑበት ግለሰብ ስልክ በመደወል መደበኛ ባልሆነ መንገድ ያለ የጽሑፍ አቤቱታ ለችግሩ መፍትሄ የሚገኝበት መንገድ ካለ ያፈላልጋል። የቅድመ-አቤቱታ ሽምግልና በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነው፤ የእርስዎን እና መልስ ሰጪ ሊሆን የሚችለውን ወገን ተሳትፎ ይፈልጋል። የቅድመ-አቤቱታ የእርቅ ውይይቶች በምስጢራዊነት የሚጠበቁ ናቸው፤ ጉዳዩ ወደ መደበኛ አቤቱታ ቢሸጋገር ግልጽ አይወጡም።

ይህ ሂደት ፈጣን እና መደበኛ ያልሆነ በመሆኑ ብዙ ወገኖች አርኪ መፍትሄ ወይም ገለጻ በዚህ ሂደት አማካኝነት ያገኛሉ። መልስ ሰጪ ሊሆን ከሚችለው ወገን ጋር እርስዎ የሚደርሱበት ማንኛውም ስምምነት ለሁለታችሁም በሚጻፍ ደብዳቤ በግልጽ የሚሰፍር ይሆናል። ይህ የሚደረገው ስለ ውሳኔው ሁሉም ወገኖች ያላቸው ግንዛቤ የተሳሳተ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ነው። ብዙ ጊዜ የስምምነቱ ነጥቦች ተፈጽመው እስከሚያበቁ ደረስ እኛ ጋር ያለው የእርስዎ የግብዓት ሰነድ አይዘጋም። መልስ ሰጪ ሊሆን የሚችለው ወገን ስምምነቱን ካልተገበረ እርስዎ እኛን ማናገር ይችላሉ፤ እኛም ጉዳዩን በድጋሚ እንመለከተዋለን።

## ችግሬን አስቀድሜ ለዩኒየኔ በማመልከት ወይም ሌላ የሕግ ሂደት በመጠቀም ተከታትያለሁ። የሰብዓዊ መብት አቤቱታ በተጨማሪ ማስገባት እችላለሁን?

ችግሮችዎን አስቀድመው በዩኒየንዎ ወይም በሌላ የሕግ መድረክ (እንደ ማኅበራዊ አገልግሎቶች ይግባኝ ቦርድ፣ የሠራተኞች ካሳ ቦርድ፣ ወይም ፍርድ ቤቶች በመሳሰሉት) ተከታትለው ከነበረ ኮሚሽኑ የእርስዎን አቤቱታ ሳይመረምረው ለመሰረዝ ሊገደድ ይችላል። ይህ አንድ ጉዳይ ከአንድ በላይ በሆኑ የሕግ መድረኮች እንዳይታይ ለማረጋገጥ እና ኮሚሽኑ የሌሎችን የሕግ ውሳኔ ሰጪ አካላት ስልጣን እንዲያከብር ለማረጋገጥ ይጠቅማል። ለበለጠ መረጃ ያዘጋጀነውን “*የመጀመርያ ምዘና እና ያለ ምርመራ መሰረዝ አጋዥ*” ይመልከቱ።

ጉዳዩን በሌላ መድረክ አስቀድመው ተከታትለው ከነበረ እባክዎ ለግብዓት ባለሙያዎ ይንገሩ። የሚቻል ከሆነ ሌሎች ድጋፍ ሰጪዎች እና ኤጀንሲዎችን ይጠቁሙዎታል።